በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከጁን 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም ከጁን 21-30 እና ከጁላይ 1-10 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁን 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ - 1 -
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 2 -
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ........ - 2 -
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ - 3 -
እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20 /2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 3 -
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 4 -
እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 4 -
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 4 -
እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ........ - 5 -
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁን 21-30, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 6 -
እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ........ - 6 -
ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10፣ 2024 ........ - 7 -
የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 7 -
እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 8 -
እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 8 -



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አሥር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በምዕራብ አጋማሽ፣ በመካከለኛው እና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከዕለት ወደ ዕለት ከመጠናከራቸው ጋር ተያይዞ በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው። ከዚሁ ጋር በተያያዘም በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 46.5፤ በአይራ 46.2 እና 53.4፤ በአለም ተፈሪ 41.4፤ በአንገርጉትን 35.0፤ በአርጆ 36.2፤ በአሶሳ 49.5፤ በደብረ ማርቆስ 36.6፤ በአይከል 30.0፤ በጭራ 41.0፤ በጊምቢ 68.7፣ 46.3 እና 31.9፤ በላይበር 56.5፤ በማሻ 40.2፤ በነጆ 30.5፤ በሰኮሩ 30.0፤ በሽሬ 35.4 እና 30.5፤ በጉብሬ 49.5 እንዲሁም በግራዋ 35.0 ሚ.ሜ. የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።


ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ሆሮ ጉዱሩ እና ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ፤ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ከትግራይ ክልል ሰሜን ምዕራብ ዞን፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ እና አኝዋክ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ፋፋን ዞን፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ጠምባሮ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ኮንታ፣ ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ እና ከፋ ዞኖች ላይ ከ30-205 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ ከአማራ ክልል ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋግህምራ፣ ሰሜን እና ምዕራብ ጎንደር፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ኤረር፣ ጀረር እና ኖጎብ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ ዞን እንዲሁም




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከ5-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ የሰሜን ምዕራብ እና ምዕራብ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ከማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዡንግ፣ አኝዋክ፣ ኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከሱማሌ ክልል ፋፋን ዞን፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ጠምባሮ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ባስኬቶ፣ ወላይታ እና ጌድኦ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች እንዲሁም ሀረር እና አዲስ አበባ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ
የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20 /2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የተሻለ እርጥበት የነበራቸው ሲሆንና ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በመሆኑም አስቀድመው ለተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ ቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሀ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም በጁን ወር ለሚዘሩ የተለያዩ የመኸር ሰብሎች ለማሳ ዝግጅት ለማከናውንም ሆነ ዘር ለመዝራት በቂ የሆነ እርጥበት እንደነበራቸው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በተጨማሪም የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት በጥቂት በምስራቅ በሚገኙ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተገኘው የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው (ካርታ 4)፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፋት አስር ቀናት በአባይ፣ ተከዜ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው አዋሽ፣ ዋቤ ሸበሌና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ተስተውሏል። ይህም ሁኔታ ለገጸ ምድርም ሆነ ለከርሰ ምድር የውኃ ሀብት መሻሻል እንዲሁም የግድቦችን እና የወንዞች የውኃ አቅም ከማሻሻል አኳያ አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በጁን ሶስተኛው አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ የሚጠናከሩበትና የሚስፋፉበት ጊዜ ነው፡፡


በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን በተሻለ መልኩ የሚጠናከሩ ሲሆን፤ በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች የዝናቡ ስርጭት በመጠንም ይሁን በስርጭት የሚስፋፋበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛው እና በሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ሰሜን  እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ አዊ፤ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ዋግህምራ፤ ከትግራይ ክልል ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ ፓዌ፤ አሶሳ እና ካማሺ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ እና አኙዋክ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ እና ፋፋን ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ሀላባ፣ ስልጤ፣ ጠምባሮ፣ ሃዲያ፣ የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ኮንሶ፣ ወላይታ፣ ጌድኦ፣ አማሮ፣ አሪ እና ደራሼ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ከዕለት ወደ ዕለት ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ቦረና፣ ጉጂ እና



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ጀራር፣ ኤረር፣ ኖጎብ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ እና ሀሪ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን እንዲሁም ከጋምቤላ ክልል ንዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁን 21-30, 2024

የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ


## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ የመጀመሪያው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አከባቢዎች የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛው እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል (ካርታ 2) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሚቀጥሉት በጁላይ የመጀመሪያው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ይበልጥ እየተጠናከሩ ይመጣሉ፡፡ ስለሆነም በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች በብዙ ስፍራዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 2) ፡፡




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10፣ 2024
የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት የሚጠበቀው የእርጥበት ሁኔታ ወቅታቸውን ጠበቀው ለሚዘሩ እና በመዘራት ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬ ተክሎች የውኋ ፍላጎት መሟልት አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። በተጨማሪም በበልግ ወቅት ተዘርተው በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችም በጎ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

በሌላ በኩል በአረብቶ አደር እና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት የግጦሽ ሳርና የመጠጥ የውሃ አቅርቦትን ከማሟላት አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። በአንፃሩም በአንዳንድ አካባቢዎች የሚጠበቀው ከፍተኛ እርጥበት በደረሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስቀድሞ የመሰብሰብ እንዲሁም ወቅታቸውን ጠብቀው በሚዘሩ እና በቡቃያ ላይ በሚገኙ የመኸር ሰብሎች ደግሞ በጎርፍ እንዳይጠረጉ የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን በማዘጋጀት አስፈላጊውን የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አፋር ደናክሌ፣ የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ተፋሰሶች የተሻለ የውሃ መጠን እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን በተጨማሪም ለመስኖም ሆነ ለሀይል ማመንጫነት የሚያገለግሉ ግዴቦችን የውሃ መጠን ከመጨመር አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et